# “ የአገር አምላክ ”

በየዕለቱ በየሰንበቱ በ‘ጁማው’ በወር በዓመቱ፤
በቅዳሴ በውዳሴ በመንዙማው ደጅ ጥናቱ፤
በየአድባሩ በገዳሙ በመስጊዱ እንደ እምነቱ፤
ጸበል-ዝክሩ ምጽዋት-‘ዘካው’የውል-እድር ስለቱ፤
መማጸኛው  ጾም-ጸሎቱ ስግደት-‘ሶልዓቱ’፤
የሚጦፈው የሚጤሰው ቁርስ ምሱ በሰዓቱ፤
‘ለአሮጌ አምላክ’ ለአድባር ቆሌው ለጥንቱ፤
‘ሀጂ’ ምነናው የመንፈስ ምልጃው ለቸርነቱ፤
‘ወደ ፈተና አታግባን’ መጽሐፈ-ቃል ግዝቱ፤
ሲጎርፍ ሀዘን አቤቱታው በየታቦቱ፤በየጣዖቱ፤
የአገር አምላክ በአገር ካለህ በሰማያቱ፤
ለምን አትፈርድም በጥዋቱ፤በጊዚያቱ፤
አንዲበቃን ቀን ‘በመለስ’ መታገቱ።

አብሮ እንዲቀበር ሞት ስጋታችን በምሽቱ፤
እንዲፈጻጸም ሁለት - ዓስርተ - ዓመታቱ፤
እንዲበየን በአገር አምላክ ሥርዓተ - ፍታቱ፤
‘ወደ ፈተና አታግባን’ መጽሐፈ - ቃል ግዝቱ፤
የፈጣሪ ቃል ዓሥርቱ እንዴት ይቀራል በከንቱ፤
ነግሶ ወርሶን ባገራችን ኃጢያቱ በምድራዊ ግዛቱ፤
የአገር አምላክ በአገር ካለህ በሰማያቱ፤
አውርድልን ሸክማችንን ‘መለስ’ ብለህ በጊዜያቱ።

የጎንቻው ! yegonchaw@yahoo.co.uk

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com